# የጌታዋን መሞት ያላወቀች አህያ፣

# ፉሩሽካ ለሰጣት ሁሉ ትጫናለች!!!

(ለአቶ አሰፋ ነጋሽ የተሰጠ ምላሽ!!!) ከእሸቴ ረጋሳ

በቅድሚያ ፅሁፌን ለሚያነቡ ሁሉ ማሳሰብ የምሻው፣ ብዕሬን ያነሳሁበት ዋነኛ ምክንያት አቶ አሰፋ ነጋሽና እሳቸውን የመሰሉ ሁሉ የዛ ትውልድ አብጠልጣዮችና የ66ቱ ዓብዮት ፀሮች በተለያየ ጊዜ የሚያቀርቡትን የሀሰት ክምርና ውሸት ለማቆም አለመሆኑን እንዲገነዘቡልኝ ነው። ይህን መሰል ውሸት የነበረና የሚቀጥልም ነው። በህብረተሰባዊ የቅራኔዎች ህግጋት ደንብም፤ ሥር ነቀል ለውጥን በሚሹ አብዮታዊ ኃይሎችና በፀረ ህዝብ ኃይሎች አሊያም ያለፈን ናፋቂ ኃይሎች መሃልም ያለ ግብግብ አከል ነው። የፅሁፌ ማዕከላዊ ሃሣብ ለእውነት መቆምና እውነት ሲደፈር፣ ተጨባጭ እውነት ሲካድ ግንባሬን ለማሳየት ነው። አቶ አሰፋ ዛሬ "ከነ አመራሩ በጀሌነት ተዋናይ የነበረው" እያሉ የሚያብጠለጥሉትንም ያን ትውልድ ልዩ የሚያደርገው ለእውነት መቆሙና እውነት ሲደፈር ውድ ህይወትን በመክፈል ከፍተኛውን መስዋዕትነት ለሀገርና ለህዝብ መክፈል መቻሉም ነው።

አቶ አሰፋ በፅሁፋቸው ዛፉን ፈርተው ቅርንጫፉ ላይ መንጠልጠልን የመረጡ ይመስላል። ችግሩ ግን፣ ቅርንጫፉ ላይ መንጠልጠል ከሞትም ከውርደትም አለማዳኑ ነው። አስተዳደግዎም ለዚህ በፅሁፍዎ ለሚያሳዩን መቀባዠር አስተዋፅዖ እንዳደረገ አምናለሁ። ይህንን ሁሉ ዝቅ ብዬ እመጣበታለሁ። ሊመሮት እንደሚችልም እገምታለሁ፣ ግን ሊክዱት የማይችሉት እውነት ስለሆነ በአግባብ እንዲጐነጩት በቅድሚያ በትህትና እጠይቆታለሁ። ለዓመታት ከድርጅት ድርጅት ከቡድን ቡድን ሲዘሉና ሁሌም ግን አሉታዊ ሚናን ሲጫወቱ የታዘብን ነንና ስራዎ ዛሬ አይገርመንም--ምንም እንኳን አንቱታን ባንነፍግዎም።

አስቀድሜ ግን እንደ እርስዎ አራምባና ቆቦ ሳልረግጥ በግንዱ ልጀምር። ዋናው ጥያቄ ያ ወርቅዬ ኢትዮጵያዊ ትውልድ ከነ አመራሩ ያነሳቸው መሠረታዊ የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄዎች ምን ነበሩ የሚለው ነው።

እነዚህ ጥያቄዎችም፦

ሀ) መሬት ላራሹ፣

ለ) የዴሞክራሲ ጥያቄ ካለገደብ፣

ሐ) ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግሥት፣

መ) የፍትህና ርትዕ መብቶች መከበር፣

ሠ) የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣

ረ) የብሄርና ብሄረሰቦች መብት መከበር

ሰ) የሴቶች እኩልነት መረጋገጥ፣

ሸ) የሠራተኛው፣ የአርሶ አደሩ፣ በአጠቃላይ የህብረተሰቡ ሁለገብ መብት መከበር፣

ቀ) የሃይማኖቶች እኩልነት መረጋገጥና፣ የመንግሥት በሃይማኖት፣ የሃይማኖቶች በመንግሥት ጣልቃ አለመግባት፣

በ) በህዝብ ዴሞክራሲያዊ እኩልነት ላይ የተመሠረተ ሀገራዊ ሉዓላዊነት መከበር … ወዘተ ናቸው።

ያ ውድና የተከበረ ትውልድ የታገለው እነዚህ ጥያቄዎች በአግባብ ተመልሰው፣ ህብረተሰባችን ዘላቂ ሠላምና መብት እንዲቀዳጅ ነው። ዛሬም የኢህአፓ አባላትና አካላት ለነዚህ መሠረታዊና ህብረተሰባዊ ችግሮች እየታገሉ ናቸው። ዛሬስ ከነዚህ መሠረታዊ ጥያቄዎች ውጭ

የምንታገልላቸው ሁኔታዎች ይኖራሉን? አይኖሩም። ሌላው አማራጭ እንደ እርሶና ግብረአበሮቾ ታጋዮችን እያብጠለጠሉ፣ ጎጠኝነትን በወያኔ ግልባጭ እያራገቡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስቃይ የሚራዘምበትን መንገድ ማመቻቸት ነው። ይመራል ግን እውነት ነውና ይጐንፈጬት፣ አእምሮ ካሎት ፈውስ ይሆኖታልና!!

በነዚህ የተራዘሙ የትግል አመታት ኢ.ሕአፓ ስህተቶች አልሰራም? አዎ! ሰርቷል፣ ግን እነዚህን መሠረታዊ ዓላማዎች አልለቀቀም። በየትግሉስ የሂደት ደረጃ እራሱን ገምግሞ ስህተቶቹን አላረመም? ገምግሞስ ትግሉን አልቀጠለም? እውነትን ለማወቅ ለተዘጋጀ ሁሉ መልሱ አዎ ነው። ይህ እውነት ግን እንደነ አቶ አሰፋና ግብረ አበሮቻቸው የሀሰት አባወራዎች የሚታይ አይደለም። በተጨማሪም እርስዎ እንደሚያስቡት፣ አብዮታዊ ጉዞ ወይም ለመሠረታዊ ለውጥ የሚደረግ ትግል ቀጥተኛ መስመር አይደለም። ብዙ ውጣ ውረድ፣ ፈታኝና እልክ አስጨራሽ፣ ትላልቅ መስዋዕቶችንና በመጨረሻም ውድ የሆነን ህይወት መክፈልን የሚያካትት፣ ዓላማውን በግልፅ አስቀምጦ፣ ህዝባዊ ዓላማና ጥያቄዎችን አንግቦ የሚደረግ ጉዞ ነው። ከኩባ በረራና ፈትለክ ጭራሽ የተለየ ነው።

ይህን በመሰለ ዕልክ አስጨራሽ ጉዞ ውስጥ፣ ገሚሱ ውድ ህይወትን ገብሮ ታሪክ ሰርቶ ያልፋል። ሀሞት ያልጐደለው ከፊል ደግሞ የቀደሙትን ታሪክ ተከትሎ፣ አብሮ ያነሳቸውን ዓርማ አንግቦ መራራውን ትግል ይቀጥላል። ሌለኛው ገሚስ ደግሞ ጤናው ተጓድሎ አሊያም በተለያዩ ችግሮች ተይዞ፣ ክብሩንና የትግሉን ዓላማ ሳያሰነካ በደጋፊነት የትግሉን አካል ሆኖ ይኖራል ወይም ያርፋል። ጥቂቱ ደግሞ የራሱን የሞራል ዝቅጠትና የአእምሮ ሠላም ማጣት መወጫው ለትግሉና ለታጋዮች ጠላት ሆኖ መቆምን አድርጎ ይወስደዋል። አቶ አሰፋ የርሶ ምድብ የት እንደሆነ እራሶ ያውቁታል፣ በፅሁፎ ላይ ግልፅ አርገው ስላስቀመጡት የምንከራከርበት ጉዳይ ይሆናል ብዬ አላምንም።

ዛሬ ባለንበት ጊዜ እርስዎም ከበራቻቻ ፅሁፎን እየበተኑ ባሉበት ወቅት፣ በጣም በርካታ ዘመቻ በኢህአፓ ላይ እየተካሄደ መሆኑን ሁሉም የሚያውቀው ጉዳይ ነው። ዋናው ጥያቄ ግን ቀደም ጥቅማችን ተነካ ይሉ እንደነበሩት ፊውዳሎችና ከበርቴዎች ዛሬ ተቃዋሚዎቹ እነማናቸው የሚለውን ሁኔታ ለማየት መቻሉ ነው። መልሱ ይነገረኝ ካሉ፦

ሀ) ወያኔና ወያኔ በስውር የሚደግፋቸው፣ ፀረ ኢህአፓ መፅሃፍ የሚያሳትምላቸው፣ በየፓልቶኩና በድህረ-ገፆች የሚያሰማራቸው፣

ለ) ባዕዳን የሚከፍሏቸውና ለብሄራዊ ጥቅማቸው በተቃዋሚ ስም የሚያሰማሯቸው፣

ሐ) ጠባብ ብሄርተኞችና እንደ እርስዎ ያሉ ትምክተኞችና ፀረ አጠቃላይ ሌላውን ህዝብ ጠይዎች፣

መ) በአጠቃላይ ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ መሰረታዊ ለውጥ ተዋንያኖች፣

ሠ) ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ ዴሞክራሲ ሃይሎች፣

ረ) ያረጀ የገለማና የሞተ ስርዓተ ማህበር ናፋቂዎች ናቸው።

ይህ ሁሉ ጫጫታ ሲካሄድ ኢህአፓ ትግሉን አቋረጠ? አላቋረጠም። በከፍተኛ ደረጃ ቀጠለበት፣ ይህ ሁኔታ የበለጠ ኢህአፓን አስተዋወቀው። ሕዝብ ቀድሞም ኢህአፓን የሚያውቀው ቢሆንም፣ የኢሕአፓ አሁንም መኖሩና ትግሉንም መቀጠሉ አስደሰተው!!!

አሰፋ! ወያኔ ሥልጣን፣ ሲይዝ እናቶችን በቀይ ሽብር የሞቱትን አስመዝግቡ እያለ ሲያላቅስ ለምን መሠሎት?። ህዝብ ደምና ነብስ ውስጥ ኢህአፓ መኖሩን ስለሚያውቅ እኮ ነው። ለኔ እርሶ ዛሬ ኢሕአፓን ሲሳደቡ፣ በዛ ትውልድ ሲሳለቁ፣ ከወያኔ የማይተናነሱ የባንዳ ባንዳ መሆኖን

አረጋጋጭ ነው። አይጥሞትም አውቃለሁ ግን እውነት መናገርን በራሴ ላይ የጣልኩት ግዴታ ነውና ይደሰቱት።

እርስዎ በፅሁፎ ውስጥ ደጋግመው ያነሱልን የታሰሩበትን ቀበሌ ነው። በዚሁ ሳቢያ በእስር እያሉ ስላገኟቸው ታጋዮች፣ ዛሬ በአብዛኛው በህይወት ባይኖሩም ጠቃቅሰዋል። ስለእነሱ ይጠይቀኛል ብለው ግን አያስቡ። ይህንን ጥያቄ ልጠይቅዎት ያልደፈርኩት የሞራልም፣ የታጋይም ባህሪ እደሌሎት ከተገነዘብኩ ስለቆየሁ ነው። ለኔ ግን የት ቀበሌ እንደታሰሩ ሳይሆን፣ እንዴትና በምን መንገድ እንደተፈቱ በቅድሚያ ቢነግሩኝ እመርጥ ነበር። ሆኖም ግን እንኳን ያኔም ቢሆን ከእሥር ተፈቱ እያልኩ ደስታዬን እገልፃለሁ። ይህን ማለቴ ግን ማን እንዳስፈታዎትና እንዴት እንደተፈቱ ባለማወቄ አርገው አይውሰዱት። በኔ እምነት ፍርድና ፍትህ በሌለበት ሥርዓት የታሰሩ ሁሉ ይፈቱ የሚል እምነትና አቋም ስላለኝ ነው። የኔ ጥያቄ ግን እነዛ እርሶና በመቶ ሺ የሚሆኑ ወጣቶችና እናቶች የታሰሩባቸው መሠረታዊ የህብረተሰባችንን ጥያቄዎች (ቀደም ብዬም የዘረዘርኳቸውን) እርሷ የት አደረሷቸው? የሚለው ነው።

ወይስ እዚህ ላነሳው በማልፈልገውና በሚወገዝም መንገድ ከእሥር በመወጣቶና በዚሁ መሰረትም ከሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወደ ኩባ በመላኮ ታስርኩላቸው ያሏቸውን ሕዝባዊ ዓላማዎች ጣሏቸውና፣ ጠሉአቸው? ወይስ እጅግ በጣም በስለውና ነቅተው እርሶ እንዳሉት "አብዮቱ ሰብዓዊ ዕሴቶቻችንን ስላጠፉ" የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄዎች በነው የጠፉ መስሎት ወደ ኩባ ኮበለሉ? አሁንስ በ እገሌ እገሊት በኩል ሌላ የመገናኛ በርና መንገድ ከፍተው ይሆን?

ፅሁፎን ልጥቀስ! መጠቀስ የማይገባዎት ብኩን ቢሆኑም። "አብዮቱ የማህበራችንን ባህልና አመለካከት ይበልጥ ኢሰብዓዊ አድርጎታል። በህግ አምላክ፣ በየኔታ በዳዊታቸው … ወዘተ የሚሉ ጠቦችንና ኃይለኞችን የምንከለከልበት ዘመን ተሻጋሪ የህሊና ዳኝነት

የተላበሱ የሃይማኖት፣ የሞርልና የህግ ዕሴቶችን አሽቀንጥሮ ጥሏቸዋል”። አቶ አሰፋ! ምነው ይኽ ሁሉ ዓመታት ካለፈ በኋላ የድንቁርና መጋረጃዎን መክፈት ተሳንዎት?? ስለ ማን፣ ስለ የትኛውስ ህግ ነው የሚያወሩን። የፊውዳሉ ቆራጭ ፈላጭ ሥርዓት ለራሱ የደነገገውንና ህዝባችን ላይ የጫነውን ህግ ነው? እርሶ በየኔታና በዳዊታቸው ብለው፣ ሊመታዎት የሞከረን ጡንቸኛ አቁመው ይሆናል። በየኔታና በዳዊታቸው የማያምነው የሌላኛው እምነት ተከታይ፣ በሼኩ በቁራን እባክህ አትንካኝ ቢል ሃይለኛው ተማቺ ይተወው ይመስለዎታል? የሃይማኖት እኩልነት ባልተከበረበት ስርዓት፣ ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ነች፣ እየተባለ በሚዘመርበት አገር። በሁለቱም ትላልቅ ሃይማኖቶች የማያምን አለያም ምንም አይነት ሃይማኖቶች የማይከተል፤ ግን ኢትዮጵያዊ ዜጋ በየኔታና በዳዊታቸው ሃይለኛ እንዳይመታው እንዲማፀን ሊገደድ ይሆን? ወይስ በርሶ የስታትስቲክ ማህደር ውስጥ ይህን መሰሉ ዜጋ የሚቆጠር አይደለም? ስለ የኔታ ሲያወሱንስ፣ ምነው ስለ እሳቸውና ዳዊታቸው ብቻ ተናግረው ቀጥ አሉ? ቀን ስንጠበጠብበት የምንውልበት አለንጋቸውንም ቢያክሉበት መልካም ነበር ወይስ ቄስ ትምህርት ቤት ያልገቡና ዳዊት ያልደገሙ (እርስዎ ዛሬ እንደሚሉት “መናፍቅ” ነበሩ? እውነትን መደበቅና ተንሻፎ መሄድን ባህሎ ካረጉ በመቆየትዎ ነው እንጂ፣ በየኔታ አለንጋ ብዙዎቻችን ተጠብጥበናል። እራሳችን ላይ እስክንሸና ማልቀስ እንኩዋን እየተከለከልን፣ በል ዋጥ አርጋት! እያተባልን ዘመናት ተካተዋል። ያቺ ፊደል የምንቆጥርባት የቀን ውሎ ልታልቅ ደርሳ ስንደሰት፣ ሲጠበጥቡን ለዋሉት ቄስ “<u>የየኔታን ጠላት በብረት ቁልፍ</u>” በሉ እንባላለን።

ችግሮቹን በመሠረታዊ ለውጥ ላንዴና ለመጨረሻም ለመፍታት ለሚሻው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና ከሱ ጋር ለወገነው አብዮታዊ ትውልድ፤ የዚህ ዓይነቱ ባህል የመጥፎ አስተዳደግ መግለጫ ነው። ስለዚህ በመሰረታዊ ለውጥ አማካይነት መለወጥ በአዲስና በበለጠ የአስተዳደግ ባህል መተካት አለበት። እርሶ የሚያሞካሹት የፊዩዳሎች ህግም እንዲሁ!!

ለእርሶዎና መሰሎቾ ግን "ከዘመን ዘመን መሸጋገር ያለበት የህሊና ዳኝነትን የተላበሱ፤ የሃይማኖት፣ የሞራልና የህግ እሴቶች ናቸው"። እርሶና መሰሎቾ ላላፊና ለደቀቀ ባህላዊና የህግ ስርዓት፣ ህይወት ለመስጠት የምትጓጉ፣ ያ ትውልድና ዛሬም ትግሉን ቀጥሎ ያለው ክፍል ደግሞ ለአዲስና ህዝባዊ ባህል፣ የፍትህና የህግ ስርዓት በህዝቦች እኩልነት ላይ ለተመሠረተ አገራዊ ሉዓላዊነት የሚታገል ኃይል ነው። ቁልጭ ያለው እውነት ይኸው ነው። ዛሬም እርሶና መሰሎቾን የሚያስለፈልፋችሁ የዚህን እውነት ፍራቻ ነው።

በአጠቃላይ የፅሁፎ ማዕከል አረገው የተነሱት፣ የነበሩትን የአገዛዝ ስርዓቶች መርምሮ፤ ምን ጐዷቸዋል? የጐደላቸው ባይኖርስ ብዙሃኑ ህዝብ ለምን አመፀባቸው? ለሚለው ጥያቄ በቅድሚያ መልስ መሻት ሳይሆን፣ የገለማውን ያረጀና ያፈጀ ሥርዓትን የታገሉትንና እየታገሉም ያሉትን ትውልድ ማብጠልጠል ላይ ነው። ዱላ ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ ይላሉ ይህ ነው። ያ ትውልድ ይህን የመሰለ አስከፊና አፋኝ አገዛዝ ይጥፉ፣ ይውደም ብሎ ሲነሳና ለውድ ህዝብና አገር ውድ ህይወቱን ሲገብር፣ እርሶና መሰሎቾ ዛሬም ለዛ አስከፊ የአገዛዝ ስርዐቶች ጥብቅና ቆመዋል። ያለቀና ያበቃ ናፋቂዎች የምትባሉትም ለዚህ ነው። በፋሽሽታዊ አገዛዝ ለተሰዉ ውድ የአገሪቱ ልጆችና ጓዶቻችንም ተቆርቋሪ ለመምሰል ሞክረዋል። ድሮም፣ ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል ይባል አይደል። እነሱ ታግለው፣ ተሰውተው ለጣሉት ሥርዐት ጥብቅና ቆመው፣ ለነሱ ተቆርቋሪ መምሰልን ኬት አገኙት። ወያኔም እኮ ገና ሥልጣን ኮርቻ ላይ ጉብ ሲል ለዛ ትውልድ ሀውልት እሰራለሁ፣ ሙዝየም ከፍቻለሁ ሲል ነበር። ወያኔንም እርሶንም ባንዳ ብል ሥህተቴ ምኑ ላይ ነው??? ባንዳ ስሎት የሰደብኮት እንዳይመስሎት፣ ለኔ ከእውነት ጋር ወግኖ መገኘት ግዴታዬ ስለሆነ ነው።

በፅሁፎ ላይ ስለብርሃነ መስቀልና ስለጌታቸው ማሩም ቀባጥረዋል። ትክክለኞች እነሱ ነበሩ፣ ብዙ ብዙም ብለዋል። የዚሁ ፅሁፈዎ ማጠንጠኛ የሆነውን  የብርሀነመስቀል የደርግ ምርመራ ፅሁፍም በግለዎ

ጎርጉረው እንዳገኙት ሁሉ "በእጃችን ስለገባ፣ ለሕዝብ ይፋ አድረገነዋል" ለማለት ደፍረዋል። ፀሐይ የሞቀው ቅጥፈት! ኢ.ሕአፓም ሆነ ሌሎች የህዝብ ወገኖች የሚያካሂዱትን ትግል አፍቃሪ በሆኑት በደብተራው፣ በአሲምባ እና በሌሎችም ድረ-ገፆች ላይ ታትሞ ብዙ ቀናት ሕዝብ ካነበበው በሁዋላ እንዳ ሲሉ ትንሽ ሀፍረት አይሰማዎትም? አዎ! ምን ይገርማል ቀድሞውንስ ባለጌ ደፋር ነው ይባል አይደል። አልገባዎት እንደሁ እንጂ የባለጌ ደፋርና፣ የጀግና ደፋር በጣም ይላያያል። የባለጌ ደፋር መለያው መዋሸት፣ መቀላመድ፣ ያልሆነን ሆኗል ማለት ሲሆን፣ የጀግና ደፋር ግን ለእውነት ቆሞ ለዓላማው መሳካት ውድ ህይወትን ጭምር ለመክፈል ፈቃደኛ መሆኑ ነው። ዛሬ ድርጅቱንና ሌሎችን ለማጥቃት ሲሉ ነው እንጂ ከዚህ ቀደምማ ብርሃነመስቀልን ሲያወግዙትና ትግሬ-ሻዕቢያ ብለው ሊያብጠለጥሉት ሲጥሩ ነበር ። ያቺን ከመጽሃፍ ብጤ አሳዛኝ ጽሑፎን ያስታውሷል!

ኢ.ሕአፓን ካወቁት ላስታውሶ፣ ካላወቁት ግን ስለአሰራሩ ልንገርዎ። ኢ.ሕአፓ ውሳኔዎችን፣ ዕቅዶቹን፣ የትግል ሥልቶቹን ጭምር የሚያስተላልፈውና የሚወስነው በኮንግሬስ/በጠቅላላ ጉባኤ/ ስብሰባ ነው። በአንድ የኮንግሬስ ስብሰባ ላይ በድምፅ ብልጫ ያለፈና የፀደቀ ውሳኔ የሚቀጥለው ኮንግሬስ እስኪጠራ ድረስ በሁሉም አባላትና አካላት ላይ ይፀናል። ማንኛውም አባል በየትኛውም የድርጅቱ መዋቅር ቢሰራ ለኮንግሬሱ ውሳኔ መተግበር ይሰራል። የተለየ ሃሳብ አለኝ የሚል አባል ካለም የልዩነቱ ነጥብ ግንዛቤ እንዲያገኝለት ውስጣዊ ድርጅታዊ ትግል ማድረግ ይችላል። የኮንግሬሱን ውሳኔ ተፈፃሚነት እያከበረ ለዛም እየታገለም ማለት ነው። የጠቀሷቸው ሁለት ግለሰቦች ከዚህ ድርጅታዊ ህግ ውጪ ቀጣዩ ኮንግሬስ ሳይጠራ ከድተው የወጡና አንጃ የሆኑ ናቸው። ከፍተኛ ጉዳትም በድርጅቱ ላይ ማድረሳቸው አገር ያወቀው ፀሀይ የሞቀው እውነት ነው። የብርሃነ መስቀልም ለደርግ ያደረገው አሳፋሪ ኑዛዜ ይህንን መስካሪ ነው። ለዚህም ነው ብርሃነ መስቀል ረዳ እንደታጋይ ኖሮ እንደ

አንጃና እንደፈረ ሞተ የተባለው። ባለፉት ጊዜያት በፃፉት ፅሁፎ ላይ በትግሬ ጥላቻዎ፣ ኢህአፓን የትግሬ መሰባሰቢያ ነው እያሉ ሲዘልፉ እንደምሳሌ የጠቀሷቸው ዘሩ ክሸንንና ብርሃነ መስቀልን ነበር። ዛሬ ደግሞ እነ ብርሃነ ናቸው ሀቀኞች ብለው ቀርበዎል። የአይጥ ምስክሯዋ ድንቢጥ እንደሚባለው ነው። የረፈደቦት የቀጣፊ ቀጣፊ ቢባሉስ ታዲያ ሥህተቱ ምኑ ላይ ነው?

ኢሕአፓ፣ በየኮንግሬሱ በዓባላት ከፍተኛ ድምፅ ባገኙ፣ የአባላትን የብልጫ ድምፅ ካላገኙ ደግሞ በአባልነት የሚሰሩ የአመራር አካል ያለው ድርጅት ነው። በዚህ መልክ የተመረጡ የአመራር አካል አባላት ደግሞ ውሳኔቸውና ተጠያቂነታቸውም የጋራ ነው። የኢሕአፓ አባላት ለድርጅታቸው ያላቸውን ታማኝነትና ፍቅር መግለጫ ከሆኑት ትላልቅ ቁምነገሮች አንደኛው ይህ ዴሞክራሲያዊ አሠራሩ ነው። እርስዎ በፅሁፎ ውስጥ ኢያሱ አለማየሁ እያሉ ሲቀባጥሩ ተልዕኮዎን በግልፅ እያሳዩን ነው። በቅርብ ጊዜ አንጃ ሆነው የወጡት፣ ጠባቦችና ትምክተኞች፣ የባዕዳን አፈቀላጤዎችና የወያኔ ስውር መልዕክተኞች፣ በኢሕአፓ የአመራር አካል አባላት ላይ ደጋግመው ሲዘምቱ ያየነው ነው። ለዚህም ማዕከላዊ ፍላጐታቸው፣ አመራሩን በመምታት ድርጅቱን ለማፍረስ ይቻላል ከሚል ከንቱ ምኞት በመነሳት ነው። እርሞን ያውጡ! ኢሕአፓ በዚህ መንገድ የሚፈርስ ለዚህ መሰል ሁኔታም እንዲመች ሆኖ የተዋቀረ ድርጅት አይደለም። ኢሕአፓ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተዋቀረ ህዝባዊና አገራዊ አላማን ማዕከላዊ ዓላማ አድርጐ የተነሳ ድርጅት ነው። አባላቱም አፋቸውን ሞልተው ድርጅታችን ጣዖት ጠራቢ አይደለም የሚሉትም ከዚህ በመነሳት ነው። ኢሕአፓ ጌታቸው ማሩን በኬሚካል አቃጥሎ በጆንያ ቋጥሮ ጣለውም ብለዋል። የት ቦታና የት ሆስፒታል አስክሬኑን አስመርምረው ከዚህ መደምደሚያ እንደደረሱ የሚታወቅ ነገር የለም። እስር ቤት ባለሁ ጊዜ እንደተነገረኝ … ወዘተም ብለዋል። እንደገባኝ ምስክር አለኝ ለማለት ያሰቡ ይመስላል። ትንሽ ሰነባብተው ደግሞ ጓድ ተስፋዬ ደበሳይንም ከህንፃ ላይ

ገፍትሮ የጣለው ኢ.ሕአፓ ነው ምስክር አለኝ እንዳይሉም እፈራለሁ!!! ዋናው ቁምነገር ግን ኢ.ሕአፓን አይክሰሱ አይደለም። ቀዳሚው ነገር ፍርድ በአግባብ ለሚሰጥበት፣ ፍትዕና ርትዕ ለሰፈነበት ህብረተሰብ መታገሉ ነው። ከዚህ አንፃር ስገመግሞት ነው ሚዛኖ ገለባ የሆነብኝ። አበው ቀድመው “በጅብ ጅማት የተጠፈረ ክራር ምንጊዜም ቢሆን ቅኝቱ ልብላህ ልብላህ ነው” ብለዋል። የርሶ ምኞት አራንባና ቆቦ እየረገጡ ኢ.ሕአፓን ለመምታት ባገጠጠ የፖለቲካ ጥርሶም ኢ.ሕአፓን ለመብላት ነው። “የነጋበት ጅብ መንገዱ አጀብ” ከማለት ውጭ ምን ለማለት ይቻላል።

አቶ አሰፋ በግልፅ ያወጧቸው ፅሁፎችን በየጊዜው የሰጧቸውን ቃለ ምልልሶች፣ ያረጓቸውን ንግግሮች … ወዘተ ሳነብ፣ ሳዳምጥ፣ ስከታተል ብዙ ጊዜ አሳልፌያለሁ። እኚህ ሰው ማናቸው የሚልም ጉጉትም ስላደረብኝ ጠያይቄአለሁ። ታዲያ ዓመተ ምህረቱ ባይታወሰኝም፣ ወደ ሚኖሩበት አገር ሆላንድ (አምስተርዳም) ከተማ ጓደኛዬን ለመጠየቅ መጥቼ፣ ስለ እርሶ ለመጠየቅና ለማወቅ የበለጠ ጥረት አረግሁ። በ15 ቀን ቆይታዬ ከዚሁ ጓደኛዬ ጋር ወደ አንድ የኢ.ትዮጵያ ምግብ ቤት እራት ልንበላ ሄደን፣ ይኸው ጓደኛዬ አሰፋ ነጋሽ እዛ የተቀመጠው ነው አለኝ። የማውቆትም ያየሆትም ሰው እንዳልሆኑ ወዲያውኑ ተገነዘብኩ። ከዛ ስንወጣ አንድ ሌላ ኢ.ትዮጵያዊ ሰው ብቻውን መንገድ ላይ ይሄዳል። ይኸው ጓደኛዬ፣ ዘሩ ክሸን የሚባለው ሰው ይህ አሁን ያለፈው ነው አለኝ። ወደ ኋላዬ ተመልሼ ፊት ለፊቱ በመምጣት የዘሩ ክሸንን ፊትና መልክ ለመጀመሪያ ጊዜ አየሁት። በማግስቱ ወደ መጣሁበት አገር ተመለስኩ። ይሄ ጉዞዬ እስካሁን የማይረሳኝ ነው። ሁለት በተለያየ ሁኔታ ላያቸው የምፈልጋቸውን ሰዎች ያየሁበት ስለነበር። ዘሩ ክሸንን ታሪኩን እንጂ በግል የማውቀው ሰው አልነበረም፣ እንዲሁ እርሶንም። ከተወሰነ ዓመት በኋላ የዘሩ ክሸንን ማረፍ ሰምቼ አዘንኩ “አፈር ይቅለልህ” ከማለት በቀር ምንም ማድረግ ስለማይቻል በዛ መልክ ተሰናበትኩት። እርሶን ግን በዛ መልክ ልሰናበትዎት ስላልቻልኩ፣ ስለ እርሶ ለማወቅ የነበረኝን ጉጉት ቀጠልኩበት። ታዲያ!

ካገር መውጣትና ለስደት መዳረግ እረፍት አይሰጥም እንደሚባለው በፈረንጆች አቆጣጠር በ2008 ዓ.ም ለአንድ ወር ተኩል ቆይታ ወደ አሜሪካ አገር ሄድኩ። በዛ ቆይታዬ በርካታ ከሀረርጌ ክ/ሀገር የመጡ ሰዎች አገኘሁ። ላገኘሁትም ሁሉ ስለእርሶ መጠየቅን አላቋረጥኩም። በዚሁ መጠያይቄ ሳቢያ ነው አንድ ሂርና የምትባለውን ትንሽ ከተማ በደንብ የሚያውቃትና አፈር ፈጭቶ ያደገባት ግለሰብ፣ አቶ አሰፋን ነው የምትለው ሲለኝ አዎ ወንድሜ ብዬ መለስኩለት።

አሰፋ ነጋሽ እኮ አባቱ የልምድ ጠበቃ የነበሩና ብዙም መሬት ያላቸው ሰው ነበሩ። አቶ ነጋሽ ብዙ ልጆችና አሽከሮችም ነበራቸው፣ ይሙቱ ይኑሩም ግን አላውቅም። አሰፋ ታላቅ ወንድምም አለው ደብሩ የሚባል አለኝ። ቀጥዬ ምንም ነገር ልጠይቀው አልፈለግሁም። ሰውነቴ ሁሉ ወረርሽኝ እንደመታው ሰው ተዝለፈለፈ። በፍልጥ እንጨት የታጠረው ትልቁ ቤታቸውና ጊቢያቸው ከፊቴ ተደቀነ፣ ከአቶ ነጋሽ ጊቢ ጐን ቤት ተከራይቶ ይኖር የነበረው የግብርና ሚኒስቴር ሰራተኛ ጓዴ ትዝታው ተመልሶ ከፊቴ ቆመ። በሂርና ከተማ ብቸኛ የሆነችውን የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ በከተማዋ እየዞረና የካርቦን ኮፒ እያዘጋጀ ገንዘብ በመለመን ያሰራው ቅዱስ ሰው (በኋላም ዳሬክተር የሆነው) ቁምነገረኛው አቶ አዳሙ ሁሉ መጡብኝ። የሂርና ቆይታዬ ከአራት ወር የበለጠ አልነበረም። በአራት ወር ቆይታዬ የኖርኩት ግብርና ሚኒስቴር ሰራተኛ የነበረው ጓዴ ቤት ስለነበር፣ የአቶ ነጋሽ ነጭ ሲናር በቅሎ ሲጫንና፣ ሁለቱ አሽከሮች እርካብ ይዘው በቅሎው ላይ ሲያወጡአቸው፣ ባርኔጣቸውን አጥልቀው ሽጉጣቸውን ታጥቀው ሁለቱ አሽከሮች በበቅሎው ግራና ቀኝ፣ አንደኛው አሽከር ጠመንጃቸውን ይዞ ከፊት ለፊት ይሮጡ እንደነበር፣ ለኔ የትላንት ትዝታ ሆነብኝ። እኔ በዛ አካባቢ የሁለት ዓመት ከአራት ወር ቆይታ አድርጌአለሁ። አብዛኛውን የተቀመጥኩት አሰበተፈሪ ቢሆንም፣ ዶባን፣ ገለምሶን፣ በሮዳን፣ ቢዩ ከራባን፣ ደደርን ጭምር አውቃቸዋለሁ። በፅሁፌ

መግቢያ ገደማ አቶ አሰፋ በአስተዳደጕም ተጐድተው ይሆናል ያልኩት ካለምክንያት አለመሆኑን አሁን ተረድተውት ይሆን??

በርግጥ ለርሶ ልነግርዎት የምችለው ሌላ ነገር፣ ከእርስዎ አባት የበለጠ ጋሻ መሬትና በዛ ሥርዐት ከፍተኛ ማዕረግም የነበራቸው ሰዎች ልጆች፣ በዛ ትውልድ ሥር ተካተው የታገሉና የተሰዉ፤ እየታገሉም ያሉ መኖራቸውን ነው። በርግጥ ያለንበት ዓለም በጥቅም ፍላጐት የተከፋፈለች ናት። ሁሉም ጥቅሙን ጥሎ ከህዝብ ጋር ይወግናል ማለት አይደለም። ከግል ጥቅሙ በላይ፣ ቆሞ ከህዝብ የወገነ በርግጥ አብዛኛው ላይሆን ይችላል። የርሶ ያረጀን ናፋቂነትና ለጥቅሞ ቋሚነት የሚያስለውጥ ግን አይደለም።

ዓለም ጠባብ፣ የናትም ሆድ ዥጉርጉር ነው የሚባልም አነጋገር አለ። አፍሪቃ ውስጥ በስደት ሳይሆን ከነባለቤቷ በሥራ የምትኖር እህትም አለችኝ። እሷን ለማየት ወደ አንድ የአፍሪቃ አገር ሄጄ ቀደም ብዬ የማውቀውን ሰው አግኝቼ እራት ጋበዘኝ፣ ጋባዤም ሰው፣ አንድ ሌላ ጓደኛውም እንደሚመጣ አስቀድሞ ነገረኝ። ሰውዬውም ሰዓቱን አክብሮ በቦታው ተገኘ። አስተዋወቀን። እኔም እንደለመድኩት የሽፋን ስም ሰጥቼ ተዋወቅሁት። ረጋ ያለ የሚናገረውን የሚያውቅ ሰው ሙሆኑን ለመገመት ጊዜ አልፈጀብኝም። ስለ አገራችን፣ ስለህዝባችን፣ ስለ ትውልድ ቦታችን፣ ስለ ድሮ ጓደኞቻችን ሁሉ እያነሳን ጥሩ ምሽት አሳለፍን። እኔ በዚህ ሁሉ ጨዋታ ስሜም የሽፋን፣ የትውልድ ቦታዬም ሌላ፣ አሁን የምኖርበትም አገር የተቀየረ ስም የያዘ ነበር። ይህ የጋበዘኝ ጓደኛዬ ይህንን የማደርግበት ምክንያት ለምን እንደሆነ ግን በደንብ ያውቃል። ያ ተጋባዥ ሰው ግን ስሙ ደብሩ ነጋሽ እንደሚባልና የሂርና ሰው መሆኑን ጭምር አስረዳኝ። ዓለምን ጠባብ መሆንና የናት ሆድም ዥጉርጉር መሆኑን ዳግም አረጋገጠልኝ።

ከላይ እንደገለፅኩት ስለርሶ ለማወቅ ምን ያህል እንደደከምኩ፣ ፅሁፎን እየተከታተልኩ በማንበብ ምን ያህል ወርቅማ ጊዜን እንዳባከንኩ የተገነዘቡኝ ይመስለኛል። መልሴ አጭር ነው፣ እውነትን ፈልፍሎ በማውጣት ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር መቆም፣ ዋሾዎችን ማጋለጥ የዛ ትውልድ ዓላማም ስለሆነ ነው። ፅሁፌ ተጀምሮ እስኪያልቅ አቶ እያልኩ ነው የጠራሆት፣ "ዶክተር" እንደሆኑና እንደሚባሉም ስቼው አይደለም። ለኔ ትምህርትና ዕውቀት፣ እውነትን መናገር፣ ለእውነት መቆምና ለእውነት መመስከር ማለት ነው። ይህን የምጠቀመው በርሶ ላይ ብቻ አይደለም፣ ዶክተር፣ ፕሮፌሰር፣ ሊቅ፣ ሊቀ ሊቃውንት የሚል የሃሰት ጋሻ ይዘው፣ ለሃሰት የሚሟገቱ በባዕዳን ተገዝተው በኢትዮጵያ ሕዝብ ቁስል ጨው የሚነሰንሱ በአሁኑ ጊዜ በርካታ እንደሆኑም ስለምረዳና፣ እያየሁ ስላለሁም ነው። በተግባርዎ፣ ከሆነ እርሶ መባልም ይበዛቦት ነበር። ግን እድሜዎን ስለማላውቅና ለኢትዮጵያ ስፊ ህዝብ ክብር ስላለኝ ዝቅ ከማድረግ በአቶነት ልጀምሮት ብዬ ነው። እንዴት ሊያልቅ ይችል ይሆን የሚለው ጥያቄ ግን በሚሰጡኝ ምላሽ የሚወሰን ነው። እኔ በግሌ እርሶ እንደ ተምሳለተ ምሳሌ የሚያዩትን "ፕሮፌሰር" መስፍን ወልደ ማርያምንም አንተ እያልኩ ነው የምፅፍበት። ለምን ቢሉኝ! የዝቅጠትም ደረጃ ስላለው፣ ከዘቀጡትም ዝቃጭ ስለሆነ ነው። የመርማሪ ኮሚሽን መሪ አባል በነበረበት ጊዜ ለደርግ ጠመንጃው በናንተ እጅ ነው ብሎ 60 የቀድሞ ባለስልጣኖችን ካለምንም ፍትህና ርትዕ ለማስገደል ተባባሪ ስለሆነ፣ በ1991 ዓ·ም ኢትዮጵያ የሚሉት ተወግደው፣ አትዮጵያ አይደለንም የሚሉትን አሰባስበው ወያኔን ለሥልጣን ሲያበቁ፣ ከዛም በኋላ ኢትዮጵያዊው አርበኛ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ግንባራቸውን ለእውነት ሰጥተው ለኢትዮጵያ ሲሟገቱ፣ እሱ "እነዚህም ልጆቻችን ናቸው፣ መቼ ጊዜ አገኙ" እያለ ሲሳለቅ የነበረ ሰው ነው። ከዛም በኋላ ወያኔን በሁለገብ ትግል መፋለም እንደሚገባ ሲነገር፣ ተቃዋሚ ነን የሚሉትን ሁሉ ለማስተባበር ያላሰለሰ ጥረት ሲደረግ ደግሞ "ዱላ ወይስ መላ" የሚል ማሰሪያና ግቡንም የማያሳይ ፅሁፉን ይዞ ብቅ አለ። ዛሬ

ዱላውንም መላውም ጠፍቶበታል፣ አድሃሪ መስመሩን ግን አልለወጠም። እርሶም እንደዚሁ። በመስፍን ላይ በሰሞኑ እየወጡ ያሉ ትችቶችን ያጠኗል!

በፅሁፎ በአጠቃላይ ያን ትውልድ የማህበራችንን ዕሴቶች ሁሉ በማጥፋት ሲወርዱበት ቆይተዋል። የምናወራው ስለኢትዮጵያ ህዝብ ከሆነ ማህብር አይባልም፣ የሚባለው ህብረተሰብ ነው። ፅሁፎን ሳነበው አባትዋ ከሚጠጡት ማህበር ጋር ተምታቶበት ይሆን ወይ እያልኩም አስቤአለሁ። እባክዎ ያርሙ! ይታረሙ። የወያኔ ግልባጭ ሆነው ወያኔን ከመታደግ ይታቀቡ። አደብ ይግዙ። የሌሎችን የአንጎል ችግር አክማለሁ ከማለትዎ በፊት የራስዎን አሳሳቢ ቅውስ ያክሙ ።

እውነት መናገርና ለእውነት መሥራት ብዙ ያደክማል። እኔም ደከምኩኝ። ስለዚህ የኔ ግጥም ሳይሆን የዛ ትውልድ በገጠመው እርሶና መሰሎቹን ሊገልፅ ይችላል በምለው የግጥሙ አንድ ክፍል ለዛሬ ልሰናባቶት፦

"አትጀምረው! ላትፈፅመው፣

አትራመድ! ላትጓዘው፣

አትነካካ! ላትጨርሰው፣

ላታጣጣም! አትቅመሰው፣

ላታጣፍጥ! አታምርረው፣

አታጥልቀው! ልታወልቀው፣

ሽፋን ላይሆን! አትልበሰው፣

ቃል አትግባ! ላታከብረው።